Minnesota Department of Health

TUBERCULOSIS (TB) PREVENTION AND CONTROL PROGRAM

# ሕክምና ለተደበቀ (ያልነቃ) የሳንባ-ነቀርሳ (ቲቢ) በሽታ ኣይሶንያዚድና ሪፋፔታይን (ኣይ.ኤን.ኤች - ኣር.ፒ.ቲ) Isoniazid and Rifapentine (INH-RPT)

የእርስዎ የሕክምና ፈተናዎች የተደበቀ (ያልነቃ) የሳንባ-ነቀርሳ በሽታ ወይም ኤል.ቲ.ቢ.ኣይ (LTBI) መኖርን ያሳያል። ይኸም ማለት ደግሞ የሳንባ-ነቀርሳ ሕዋሳቶች (ጀርሞች) በሰውነትዎ ጋር ስላሉ ሊያሳምምዎት ይችላሉ።

የሳንባ-ነቀርሳ ሕዋሳቶቹ ኣሁኑ ኣይጎድዎትም ወደ ሌላ ሰዎችም ኣይተላለፉም። ሕዋሳቶቹ ተኝተዋል እንደማለት ነው። ኣንዴ የሳንባ-ነቀርሳ ሕዋሳት ከነቁ ግን ሊያስታምምዎት ይችላሉ። ይኸም የነቃ የሳንባ-ነቀርሳ በሽታ (ቲቢ) ይባላል።

## የነቃ የሳንባ-ነቀርሳ በሽታን (ቲቢ) እንዴት መከላከልን እችላለሁ?

የነቃው የሳንባ-ነቀርሳ በሽታ እንዲከላከሉ መድኃኒት መውሰድ ይችላሉ። ኣይሶንያዚድና ሪፋፔታይን (Isoniazid and Rifapentine (ኣይ.ኤን.ኤች - ኣር.ፒ.ቲ) የሚባሉ መድኃኒቶች ኣብሮ ሲወሰዱ ንቁ የሳንባ-ነቀርሳ በሽታን ያክማሉ (ይከላከላሉ) ። እርስዎ ከመታመምዎ በፊት የተኙትን የሳንባ-ነቀርሳ ሕዋሳት ይገድላሉ። የሳንባ-ነቀርሳ ሕዋሳቶች በጣም ብርቱ ስለሆኑ መድኃኒቱ ሕዋሳቶችን ለመግደል ኣያሌ ወሮች ሊውስድ ይችላል።

የ ኣይ.ኤን.ኤች - ኣር.ፒ.ቲ (INH-RPT) መድኃኒት ለመቀበልና ለመዋጥ በሳምንት ኣንድ ጊዜ ከሓኪምዎ ወይም ከነርስ ጋር ይገናኛሉ። መድኃኒቱን ያለምግብ መዋጥ የተሻለ ነው። የሆድ ጭንቀት ሲሰምዎት ግን ትንሽ ምግብ መውሰድ ይቻላል።

## ሳልታመም ለምን መድኃኒቱን መውሰድ (መዋጥ) ኣለብኝ?

ተኝተው ያሉትን (ያልነቁ) የሳንባ-ነቀርሳ ሕዋሳቶች ነቅተው እርስዎን ከመስታመምዎ በፊት ሕዋሳቶቹን መግደል ይቀላል።

## ምንድነው መድኃኒቱን ባይውጥስ? (ምን ያስከትላል)?


የ ኣይ.ኤን.ኤች - ኣር.ፒ.ቲ (INH-RPT) መድኃኒትን ካልዋጡ (ካልወሰዱ)፣ ወይም ብዙ ቀኖች ሳይውጡ ሲቀሩ፣ ወይም ሓኪምዎ ወይም ነርስ መድኃኒቱን መዋጥ እንዲያቋርጡ ሳይነግርዎት ካቋረጡ፤ በ ነቃው የሳንባ-ነቀርሳ በሽታ ሊታመሙ ይችላሉ። የእርስዎንና የቤተሰብዎን ጤና የተጠበቀ እንዲሆን የቲቢ ሕዋሳቶችን መግደል በጣም ኣስፈላጊ ነው።

## ምንድነው የቢ.ሲ.ጂ (BCG) ክትባት ቢኖርኝ?

የ ቢ.ሲ.ጂ (BCG) ክትባት ለህጻናት ከብርቱ ዓይነት የሳንባ-ነቀርሳ በሽታ ለጥቂት ዓመታት ሊከላከል ይችላል። ከ ኤል.ቲ.ቢ.ኣይ (LTBI ያልነቃ የሳንባ-ነቀርሳ በሽታ) ወይም ከነቃ የሳንባ-ነቀርሳ በሽታ ለመከላከል ግን ኣይችልም። የ ቢ.ሲ.ጂ (BCG) ክትባት ቢኖርዎትም የራስዎንና የሌሎችን ጤና እንዲጠብቁ የ ኤል.ቲ.ቢ.ኣይ (LTBI) መድኃኒት መዋጥ ኣለባቸው።

## ለ ኣይ.ኤን.ኤች - ኣር.ፒ.ቲ (INH-RPT) መክፈል ባይችልስ?

ከሚነሶታ የጤና ጥበቃ የሳንባ-ነቀርሳ ፕሮግራም፡ ነጻ የቲቢ መድኃኒት ለማግኘት፡ ሓኪምዎን ወይም ነርስዎን ይጠይቁ።



## ወደ ሌላ ሰፈር ቢለቅስ?

ወደ ሌላ ከተማ ወይም ክፍለ-ሃገር ከመሄድዎ በፊት ሓኪምዎን ወይም ነርስዎን ይንገሩ። ሰፈራችሁን ከለቀቃችሁ በኋላ የቲቢ መድኃኒት ያለማቋረጥ እንድታገኙ ዘንድ ይረዳሉ።

## ስለ ኤል.ቲ.ቢ.ኣይ (LTBI) መድኃኒት ምን ማወቅ ኣለብኝ?

- ቢራ፣ ጠጅ፣ ወይም የኣልኮል መጠጥ፣ የ ኤል.ቲ.ቢ.ኣይ (LTBI) ሕክምና እስከሚጨርሱ ድረስ እንዳይጠጡ። የ ኤል.ቲ.ቢ.ኣይ (LTBI) መድኃኒት እየዋጡ የኣልኮል መጠጥ ከጠጡ ጉበትዎን ሊጎዱ ይችላሉ።
- ሌላ ዓይነት መድኃኒቶች የሚወስዱ ከሆኑ ሓኪምዎን ይንገሩ።
- ኣይ.ኤን.ኤች - ኣር.ፒ.ቲ ን በምትወስዱበት ጊዜ ከነፍሰ-ጡርነት ይጠንቀቁ። ነፍሰ-ጡር መሆናቸውን ካወቁ ተሎ ወደ ሓኪምዎን ወይም ወደ ነርስዎን ይደውሉ።

**ኣብዛኛው ሰዎች ኣይ.ኤን.ኤች - ኣር.ፒ.ቲ ን ያለ ምንም ችግር ይውጣሉ። ኣንዳንድ ሰዎች ግን ይኸንን የመሰለ ችግሮችን ይኖራቸዋል፣**

- ትኩሳት፣ ከሶስት ቀን በላይ
- ኣነስተኛ የምግብ ፍላጎት ወይም የድካም ስሜት
- የሆድ ጭንቀት ወይም ማስመለስ (መትፋት)
- የሆድ ውጋት ወይም ቁርጠት
- ጥቁር ሽንት (የሻይ ወይም የቡና ቀለም)
- ብጫ ቆዳ ወይም ብጫ ዓይኖች
- የቆዳ ችፍ ማለት ወይም እከክ
- ደንዛዛ ወይም ኣሳካኪ እጆችና እግሮች

**ከዚሁ ሁሉ ችግሮች ኣንዲት ችግር ካላችሁ፣**

1. መድኃኒቱን መዋጥ ያቋርጡ
2. ተሎ ወደ ሓኪምዎን ወይም ወደ ነርስዎን ይደውሉ። ለሚመጣው ቆጠሮን እንዳትጠብቁ።



መድኃኒትዎን ሓኪምዎን ወይም ነርስዎን እንደነገርዎት ይዋጡ። ብዙ ቀኖች ሳይውጡ ካሳለፉ፣ መድኃኒቱ ላይሰራ ይችላል።

የህክምና ቆጠሮኣችሁን ኣክብሩ። ሓኪምዎን ወይም ነርስዎን ሕክምናችሁን በመልካም እንዲራመድ ይረዳሉ።

የሚመጣው የ ቲቢ ሕክምና ቆጠሮ፣

ቀን፣

ሰዓት፣

ሓኪም ወይም ነርስ፣

ቦታ፣

ቴሌፎን፣

Minnesota Department of Health
Tuberculosis (TB) Prevention and Control Program
P.O. Box 64975, St. Paul, MN 55164-0975
651-201-5414
www.health.state.mn.us/tb